# ምርመራ ማድረግ ያለብኝ መቼ ነው? የታመመ የቤተሰብ አባል

## ጽሁፍ

[አነቃቂ ሙዚቃ]

[ትረካ]

የ COVID-19 ምርመራ ማድረግ ያለብዎት መቼ ነው?

በእርስዎ ቤተሰብ ውስጥ የሆነ ሰው በ COVID-19 ታሟል። እነርሱ እቤት ውስጥ ቆይተዋል (ራሳቸውን አግልለዋል)፣ ነገር ግን እርስዎ በቤት ውስጥ ከእነርሱ ጋር አብረው ነበሩ።

የምርመራ ምክሮች እንደሚሉት ቤት ውስጥ COVID-19 ያለበት ሰው አጠገብ ከሆኑ በኋላ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ምርመራ ማድረግ አለባቸው ።

የታመመው ሰው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሌሎችን ሊበክሉ ስለሚችሉ ቢያንስ ለአምስት ቀናት በቤት ውስጥ መቆየት እና ከሌሎች መራቅ አለባቸው። በተጨማሪም ቤት ውስጥ ሌሎች ጋር ሲሆኑ ጭምብል ማድረግ አለባቸው። አሁንም የህመም ምልክቶች ካላቸው ወይም ጭምብል ማድረግ ካልቻሉ ረዘም ላለ ጊዜ በቤት ውስጥ መቆየት ያስፈልጋቸው ይሆናል።

COVID-19 ካለብዎ ለምን ያህል ጊዜ ቤት ውስጥ እንደሚቆዩ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ከታመሙ የሚለውን ድህረገጻችንን (https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/sick.html) ይጎብኙ።

COVID-19 ካለበት ሰው ጋር የሚኖሩ ከሆነ፣ የታመመው ሰው መገለሉን ካጠናቀቀ በኋላ ለይቶ ማቆያ ውስጥ መሆን ይኖርብዎታል። በሌሎች ዙሪያ ማስክ ስለማድረግ እና ለምን ያህል ጊዜ በቤት ውስጥ እንደሚቆዩ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የMDHን የቅርብ ንክኪዎች እና ለይቶ ማቆያ ድህረ-ገጽን ይጎብኙ።(https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/close.html)

የታመመው ሰው መገለሉን ካጠናቀቀ ከአምስት ቀናት በኋላ ማንም ሰው በቫይረሱ አለመያዙን ለማረጋገጥ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ምርመራ ማድረግ አለባቸው። በዚህ ሁኔታ ለቤተሰብዎ አባል የመጨረሻው የመገለያ ቀናቸው ሃሙስ ነው። ሁሉም የቤተሰብ አባላት ከአምስት ቀናት በኋላ ባለው በሚቀጥለው ማክሰኞ ምርመራ ማድረግ አለባቸው።

በሌሎች ጊዜዎች መመርመር እንዳለብዎት እና የት እንደሚመረመሩ የበለጠ መረጃ ለማወቅ የMDH CPVID-19 መመርመሪያ ድህረ ገጽን ይጎብኙ። (https://www.health.state.mn.us/diseases/coronavirus/testsites/index.html)

[አነቃቂ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

2/2/22 (Amharic)

*ይህን መረጃ በተለያየ ቅርጸት ለማግኘት፣ በሚከተለው ይደውሉ፡- 651-201-4989*